# የአሌክሳንድሪያ ከተማ የኪንግ ስትሪት፣ ካላሃን ድራይቭ እና የረሰል ሮድ አገናኝ መንገድ የማሻሻያ ግንባታ ፕሮጀክትን በሂደት ላይ ያለው ክንዋኔ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ **የኪንግ/ካላሃን/ረሰል አገናኝ መንገድ የማሻሻያ ግንባታ ፕሮጀክትን ጥቅምት** ጀምሮ ያከናውናል። ይህ ፕሮጀክት የአሌክሳንድሪያ ከተማ የኪንግ ስትሪት፣ ካላሃን ድራይቭ እና የረሰል ሮድ አገናኝ መንገድ ዲዛይን በአዲስ መልክ የሚዘጋጅበት ሲሆን፣ በውጤቱም ለሁሉም የመንገድ ተጠቃሚዎች የተሻለ እንቅስቃሴን፣ ተደራሽነትን እና ደህንነትን ይፈጥርላቸዋል፣ እንዲሁም የአሌክሳንድሪያ ዩኒየን ስቴሽን እና ኪንግ ስትሪት ሜትሮ ስቴሽን ተደራሽነትን የተሻለ ያደርገዋል። በተጨማሪም ፕሮጀክቱ የትራፊክ መጨናነቅን ለመቀነስ የሚያስችል መልእክት የሚያስተላልፍበትን ጊዜ ያሻሽላል።

የግንባታ ሠራተኞች ከሰኞ እስከ አርብ፣ ከ7 a.m. እስከ 6 p.m.፣ እና ቅዳሜ፣ ከ9 a.m. እስከ 6 p.m. በቦታው ላይ ሊገኙ ይችላሉ። በመንገድ እና የእግረኛ መንገድ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር የግንባታ እንቅስቃሴ ከሰኞ እስከ አርብ ከ9 a.m. እስከ 3:30 p.m. እና ቅዳሜ 9 a.m. እስከ 4 p.m. ብቻ የተገደበ ነው። ነዋሪዎች እና ተሳፋሪዎች ሊያጋጥም የሚችል መዘግየትን የሚያቻችሉበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

የአካባቢ ነዋሪዎች ስለዚህ ፕሮጀክት የበለጠ እንዲያውቁ በኪንግ እና የኮመንዌልዝ መሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት እሮብ፣ ጥቅምት 4 በአሌክሳንድሪያ ዩኒየን ስቴሽን፣ 110 ካላሃን ድራይቭ ከ 5 እስከ 7 p.m. በሚደረገው ውይይት እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። ። በቨርጂኒያ የመንገደኞች ባቡር ባለስልጣን (VPRA) እና በቨርጂኒያ የባቡር ሀዲድ ኤክስፕረስ (VRE) በጋራ እየተስተናገደ ያለው ይህ ዝግጅት በኪንግ ስትሪት እና በኮመንዌልዝ አቨኑ አካባቢ ስለሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ህዝቡ እንዲያውቅ እድሉን ይፈጥራል። ስለዚህ ክንውን እና በዚህ አካባቢ እየተካሄዱ ያሉ ሌሎች ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በ alexndriava.gov/go/4904 ማግኘት ይቻላል።

የኪንግ/ካላሃር/ረሰል አገናኝ መንገድ የማሻሻያ ግንባታ ፕሮጀክትን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ በፕሮጀክቱ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡- alexandriava.gov/go/2602.

ለጥያቄዎች እና አስተያየቶች በቀጣይ አድራሻ መላክ ይችላሉ፡- ረጅናልድ ኤም. አርኖ፣ ፕሮጀክት ስራአስኪያጅ (Reginald M. Arno, Project Manager) Reginald.Arno@alexandriava.gov.